# “እሳት፡የፈጀው፡ምድጃ፡አይራመድም”።

፩-፫

ጥቅምት፡’፲፩፡ቀን፡፪ሺ፬፡ዓመት፡ምሕረት።






የምሽት፡ፀሐይ፡ጅብ፡አስፈጅ፡ትብባላለች።ብርሃኑ፡ነጋና፡አንዳርጋቸው፡ጽጌም፡የዚያው፡ብጤዎች፡ናቸው።ከቀድሞ፡ትግል፡የትግሬ፡ወያኔዎች፡አጋሮቻቸው፡የተለዩ፡ዕቅድ፡እንደሌላቸው፡ድርጊታቸው፡ይመሰክራል።ደርግ፡ተዳከሞ፡የትግሬ፡ወያኔዎች፡ወሬ፡ሲሰማ፣ቶሮንቶ፡ስብሰባ፡ተደርጐ፡በሥነ፡መንግሥታዊ፡ፈሊጥ፡(ፖለቲካ)፡ብስለት፡ያላቸው፡የትግልም፡ሥልት፡ዐዋቂ፡ሀገር፡ወዳድ፡ኢትዮጵያውያን”፤ደርግ፡ተዳከሚልና፡በአስተዳደሩ፡ውስጥ፡ገብተን፡ሌላ፡የማናውቀው፡እንዳይገባ፡መከላከል፡እንችላለንና፡የትግሬ፡ወያኔዎችን፡መደገፉ፡አደገኛ፡ይሆናል”፡በሚል፡አስተያየት፡ተለግሶ፡የነበረውን፡አስመሳዮች፡ሰርግገው፡ገብተው፡ኖሮ፡”የፈለገው፡ቢመጣ፡ከደርግ፡አይብስም፡በማለት፡ሐሣቡን፡ተቃዋሚው፡በመብዛቱ፡እንሆ!፡እንደ፡ተባለው፡ለሃያ፡ዓመታት፡በመሰቃዬት፡ላይ፡አልለን፡።በዚህ፡ምክንያት፣ብርሃኑ፡ነጋና፡አንዳርጋቸው፡ጽጌንም፡ምንም፡ቢከፉ፡ከትግሬ፡ወያኔ፡አረመኔ፡አምባገነኖች፡አይከፉም፡ብላችሁ፡ለምትደግፏቸው፡የሀገና፡ወገን፡ህልውና፡ነውና፡አስተሣሠባችሁን፡እንድታስተካክሉ፡በእግዚአብሔር፡ስም፡እንማጸናለን።



አረመኔው፡የትግሬ፡ወያኔ፡አምባገነን፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ሰው፡መሳይ፡አውሬ፡በቅልብ፡የትግሬ፡እረኞቹ፡እየተጠበቀ፡አገርና፡ወገንን፡ያወድማል፣ያሰቃያል፣ያሳሥራል፣ያስገርፋል፣...............ያስገድላል።በቀብር፡ግዜ፡ያዘነ፡ሰው፡በመምሰል፡ከኀዘንተኞች፡ጋራ፡በመቆም፡ይታያል፡እያሉ፡ለእርሱ፡ቅርበት፡ያልላቸው፡ያወሩለታል።እንደዚህ፡ያለውን፡አውሬ፡ጓደኛቸውን፡ነው፡ለይስሙላ፡ብርሃኑና፡አንዳርጋቸው፡አመሪካና፡ኢንግላንድ፡ተቀምጠው፡ልናሰውግደው፡ታጥቀናል፡እያሉ፡በውሸትና፡ቅጥፈት፡የሚደልሉ።sስለዚህ፡በተደጋጋሚ፡ቸልተኝነት፡እንዳንታለል፡እንጠንቀቅ።

የትግሬ፡አረመኔ፡አምባገነን፡ወያኔዎች፡ለባሕረ፡ምድር፡መገንጠል፡ወኪል፡ሆነው፡ኢትዮጵያ፡ባሕረ፡ምድርን፡በቅኝ፡ትገዛለች፡ብለው፡በአምባገነኑ፡አረመኔ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ለተባበሩት፡መንግሥታት፡ገንጥሉልን፡ብሎ፡የዕውቅና፡ደብዳቤ፡በመጻፍ፡አስገነጠሉ።ትግራይ፡በሚል፡ጥንት፡ያልነበረና፡የማነውቀው፡ቃል፡ፈጥረው፡እያደነቆሩን፡ነው።ኢትዮጵያን፡እኛ፡ካልገዛናት፡እንበጣጥሳታለን፡ብለው፡እንሆ!፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡መንግሥት፡አልባ፡ለሃያ፡ዓመታት፡እራሱን፡በራሱ፡በማስተዳደር፡ላይ፡ነው።የእኛን፡አስተዳደር፡የማትደግፉ፡ከሆነ፡ሥራም፡ሌላም፣ሌላም፡ዕድል፡አታገኙም፡እያሉ፡አይደለም፡እንዴ!?።

ብርሃኑ፡ነጋና፡አንዳርጋቸው፡ጽጌስ፡ምን፡ሲያደርጉ፡ታያላችሁ?።ይኸው፡እንገነጠላለን፡ከሚሉና፡አነ፡ኃይሌ፡ፊዳ፡ባጐረሷቸው፡ኦሮሞ፡የሚል፡ስምተነው፡የማናውቅ፡ቃል፡እያኜኩ፡አይደለም፡እንዴ!?።እነሱስ፡የቅኝ፡ግዛት፡ጥያቄ፡ብለው፡ፅንሰ፡ሐሣባቸውን፡አንግበው፡የሚያወናብዱ፡ወንበዴዎች፡አይደሉም፡እንዴ!?።እኛ፡ካላዘዝናችሁ፡የሚልን፡የትግሬ፡ወያኔዎች፡አባባልን፡ወርሰው፡አይደለም፡እንዴ!?።መማርን፡ትርጉሙ፡የልለሽ፡ሊያደርጉ፡ያሠቡ፡ሥልጣን፡አምላኩ፡መሆናቸው፡አይሰማች ሁምን?።ከነ፡አካቴውም፡የቀድሞ፡ጓዶቻቸውን፡ወያኔዎች፡ላለማለት፡"ግንቦት፡ሃያወችን፡ተቃወሙ"፡እያሉ፡በመሆኑ፡የብርሃኑንና፡አንዳርጋቸውን፡የእግዚአብሔር፡የለሽነት፡ስልተ፡ትግል፡ለመጠራጠር፡ተገድደናል።

እንደ፡ግምታችንም፤የትግሬ፡ወያኔው፡አረመኔ፡አምባገነን፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ወሮበሎቹ፡ሲሞቱ፡ከለንደን፡ገሥግሦ፡መጥቶ፡ወበር፡ላይ፡ተቀምመጠ።ብርሃኑና፡አንዳርጋቸውም፡አንዴ፡በተራራ፡ለሱባኤ፡ገብቼ፡ነበረ።በሌላ፡ግዜ፡የማዘጋጀው፡ጥናት፡አልለኝ፡በሚል፡ሲዘባጥር፡ተሰምቷል።

ወገኖች፡ሆይ!፦ምን፡ነካን?።ለሃያ፡ዓመታት፡በተለከፉ፡ውሾችና፡ጓደኞቻቸው፡እየተፈራረቁ፡እንጫወትባችሁ፡ሲሉን፡እንዴት፡በግዴለሽነት፡ልናልፈው፡ይገባናል?።አገር፡እዬተሸጠ፤ሕዝብ፡በርሃብ፡እያለለቀ፤የጐሠኛ፡አስተዳደር፡ተብዬ፡አቋቁምናል፡ብለው፡ከትግሬ፡በቀር፡ሌላው፤ወገን፡እንዳይሠራና፡ልጅ፡እንፍዳይወልድ፡እዬተኮላሸና፡ሕፃናት፡እስተ፡ሃያ፡ሺ፡ብር፡ለጉዲፈቻ፡እዬተሸጡ።አካላቸው፡እዬ፡ተቆረጠ፡መመራመሪያና፡አካል፡ለጐደላቸው፤መተኪያ፡ሲሆን፤ለግብረ፡ሰዶም፡ሲጋልለጡ፡እዬታዬ፡ተቃዋሚ፡ነን፡የሚሉና፡በምክር፡ቤቱ፡ውስጥ፡የሕዝብ፡ተወካዮች፡አፋቸውን፡የተለጐሙት፡ለምንድን፡ነው?።ይኸን፡የመሳሰለውን፡አጻያፊ፡ተግባር፡የሚያከናውኑት፡በሰሜን፡አመሪካና፡አውሮፓ፡ነውና፡ክብርት፡ሊቋ፡የሰብዓዊ፡መብት፡ረዳኢት፡የጉዲፈቻ፡ሕፃናት፡እናት፡አበበች፡ጐበና፡በሌለ፡ዐቅማቸው፡ሲጮሁ፣ሲቆጩ፣ሲቆረቆሩና፡ሲያለቅሱ፡ብርሃኑና፡አንዳርጋቸው፡ተቃውሞ፡አላሳዩም።ከወያኔዎች፡ጋራ፡አብረው፡አድገው፡ሲዶልቱ፡ከነበረበት፡ያልለፈ፡ዘዴ፡ቅጥፈትና፡ውሸት፡ሊያምታቱና፡ለሥልጣን፡መያዝ፡እቅዳቸው፡ከማሰብ፡በቀር።።"የቸገረው፡እርጉዝ፡ያገባል"፡እንደሚሉት፡የሰው፡ልጆች፡በጭንቀት፡ግዜ፡የማይሆኑት፡የልለምና፡በደርግ፡ተማርረን፡ዓይኖቻችንና፡አዕምሯችንን፡ጨፍነና፡ደፍነን፡ወገኖቻችንና፡ሰወች፡መስለው፡ታይተውን፡የበሩትን፡ወያኔዎች፡አስገብን፡ለሃያ፡ዓመታት፡ሥቃይ፡ዳርገውን፡ካዬናቸው፡በኋላ፡ደግሞ፡ከነጓዶቻቸው፡አሻፈረን፡የማለት፡መብትና፡ክህሎት፡አልለንና፡በኅብረት፡እንበርታ።

የሰሞኑን፡ዜና፡በትካዜ፡ስናላዝንበት፡የሰነበትነው፡ሐና፡በምትባል፡የ፲፫፡ዓመቷ፡ወጣት፡አሟሟት፡ምክንያት፡ነበረ።መቼም፡የአረመኔው፡አምባገነን፡ወያኔው፡ለገሠ፡ዜናሚ፡የነጠቃ፡አስተዳደር፡ተብዬው፡ገንዘብ፡እስታገኜ፡ድረስ፡የማይሠራን፡የልለማ!፣ሕፃናት፡ከኢትዮጵያ፡በጉዲፈቻ፡ወደ፡ውጭ፡እየተላኩ፡አካላቸውን፡ይቆራርጡታል።እያወላለቁ፡ለህክምና፡ችግር፡ላለባቸው፡መለወጫ፡ይወስዷቸዋል።እንደዚህ፡ዓይነቱን፡ተግባር፡ተቆጣጣሪ፡በሌለበት፡መንገድ፡ሕፃናት፡እስተ፡ሃያ፡ሺ፡ብር፡በመሸጥ፡ላይ፡ናቸው፡የተባለውንና፡ሲያትል፡ዋሽንግተን፡ሞታ፡በተገኘችው፡ሐና፡እናሳድጋታልለን፡ብለው፡አምጥተው፡ለሞት፡በዳረጓት፡ባልና፡ሚስት፡የቀረበባቸውን፡ክስስ፡በተቆርቋሪ፡ኢትዮጵያውያን፡ክትትል፡እንደሚያደርጉ፡በተሰራጨው፡ወሬ፡ነበረ።የአረመኔው፡ከሓዲ፡አምባገነን፡ለገሠ፡ዜናዊ፡የሸፍጥ፡አስተዳደር፡ግን፡ጆሮ፡ዳብባ፡ልበስ፡ማለቱን፡ተቃዋሚ፡ነን፡የሚሉት፡ጥንታዊ፡ጓዶች፡በርሃኑ፡ናጋና፡አንዳርጋቸው፡ጽጌ፡ለሥልጣን፡ከመሻኮት፡በስተቀር፡እንደዚህ፡ላለው፡የሕፃናት፡እልቂት፡አሰቃቂ፡ዜና፡እንኳ፡ተቃውሞ፡አላስሰሙም።

ይድረስ፡በውጭ፡አገር፡ስድደት፡ዓለም፡ኗሪ፡ለሆናችሁት፡ኢትዮጵያውያን፡ወገኖቻችን፡-እግዚአብሔር፡ሰላምን፣ነፃነትንና፡ፍትሕን፡እንዲያሣሥባችሁ፡ልብባዊ፡ምኞታችንን፡እናስተላልፋልለን።ይኸን፡ካልን፡በኋላ፣ሀገር፡ቤትም፡ሆነ፡ውጭ፡አገር፡የአረመኔው፡አምባገነን፡ከሓዲው፡ለገሠ፡ዜናዊ፣፡የቅሚያ፡አስተዳደር፡ተቃዋሚ፡ነን፡ለሚሉ፡ጥገቶች፡ሆነን፡ምንም፡

ፉይዳ፡እስታሁን፡ላልሠሩ፡ጠለላና፡ደጋፊ፡ሆነናል።ብርሃኑና፡አንዳርጋቸው፡እንደነ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ከእኛ፡ጋራ፡አብራችሁ፡ከልሥርራችሁ፡ገንዘብ፡አንሰጣችሁም፡እያሉ፡ማንጋራገራቸውን፡ምን፡ልንለው፡ነው?።

ስለዚህ፡በማጠቃለያችንም፡ስንገመግም፣ብርሃኑ፡ነጋና፡አንዳርጋቸው፡ጽጌ፡በባሕረ፡ምድር፡መገንጠል፡ካለ፡መፀፀት፡አልፎ፤ከተንገጣዮችና፡ኢትዮጵያን፡በቅኝ፡ገዥነት፡ከሚፈርርጁ፡ጋራ፡በመሰለፍ፡ኢትዮጵያ፡አገራችንን፡ለሌላ፡የሕዝብ፡ፍልላጐት፡ላልሆነ፡ግንጠላ፡እያዘጋጁን፡ለመሆናቸው፡ፍንጭ፡ይታያል።በትግሬ፡ወያኔዎች፡ዘር፡ለይቶ፡የጅምላ፡ግድያ፡ሲፈጸም፡በሥልጣን፡ሆነው፡ተቃውሞ፡ባለማሳዬታቸው፡ደጋፊ፡ላለመሆናቸው፡አላስታወቁንም።ሕዝብን፡የሚከፋፍልም፡ጽሑፍ፡በመጻፍና፡በእግዚአብሔር፡የልለሹ፡ሥርዓተ፡አስተዳደር፡አምነው፡የተጠመቁ፡ለምሆናቸው፡በኩራት፡ይናገራሉና፡ከኢትዮጵያውያን፡እምነት፡ጋራ፡ስለ፡እሚጋጭ፡ተስማሚ፡ቦታ፡የልላቸውም።እናም፣ከእባብ፡እንቁላል፡እርግብ፡ይፈለፈላል፡ተብሎ፡አይታለምምና፡ከዚህ፡ቀድደም፡ሥልጣን፡ላይ፡ላልነበሩና፡በዝምምታ፡ላሉና፡ክህሎቱ፡ላላቸው፡ምሁራን፡ዕድል፡ተሰጥቶ፡ሀገራችንንና፡እራሳችንን፡ነፃ፡ለማውጣት፡ተግተን፡መተባበርና፡በቆርራጥነት፡መታገል፡ይኖርብብናል።በአንጻሩም፤ቅንጅትን፡በመከፋፈል፣አብረውት፡ይሠሩ፡የነበሩትን፡በማጋጨትና፡የ፲፯ቱን፡የሕዝብ፡ዐመፅ፡ብርሃኑ፡ከአጋሮቹ፡ጋራ፡ፈርሞ፡በማኮላሸቱ፡ጥፋቱን፡አምኖ፡ሕዝብን፡ይቅርታ፡ሳይጠይቅ፡አሁንም፡እኔ፡የላቅሁ፡ነኝ፡እሚል፡ገታራነት፡ጠባይ፡ያልለው፡በመሆኑ፡ሥልጣን፡ይዞና፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡አስተባብሮ፡ዘረኝነትን፡በማጥፋት፡ይጠቅማል፡በሚል፡እንዳንሞኝ፡በቅድሚያ፡ይታሠብበት።ለዚህም፡ነው፡የደርግና፡ወያኔው፡ተልካሻ፡አስተዳደር፡የተሻለ፡በመመኜት፡“እሳት፡የፈጀው፡ምድጃ፡አይራምመድም፡ብለን”፡ይህችን፡ማሣሠቢያ፡ለመጻፍ፡ያቀድነው።“እሳት፡ካየው፡ምን፡ለዬውም”፡ነውና፡ኢትዮጵያና፡ሕዝቧ፡የሚፈልጉት፡ከጐናቸው፡ቁሞ፡የጐሣ፡ሥርዓተ፡ቀማኞችን፡አስተዳደር፡አስከትሞ፡አንድነትን፡ዐውጆና፡ስለ፡ምጣኔ፡ሃብት፣ኅብረተሰብ፡አድደረጃጀትና፡አኗኗር፡ማሻሻል፣ሥነ፡መንግሥታዊ፡ሉዓላዊነት፡ድክመቱንና፡ጥንካሬውን፡በመለዬት፡ዐውቆ፡፤የማይሆንለት፡ከሆነ፡አስታውቆ፡ብቃት፡ላለው፡በፈቃዱ፡ከሥልጣን፡ወርዶ፡ሰላም፣ነፃነትና፡ፍትሕ፡እንዲሰፍን፡ዕውነተኝ፡መሪን፡ነው።እንጂ፣ውጭ፡አገር፡አድፍጦ፡የውሸት፡ስብከት፡እያናፉ፡ጣታቸውን፡ቀሥስረው፡አምባገነኖችን፡እናስወግዳልለን፡የሚሉትን፡አታላዮች፡አይደልለም።የሚበጀውም፡ከሕዝብ፡አጠገብ፡ሆነው፡ዓይን፡ለዓይን፡እዬ፡ተያዩና፡እዬ፡ተመካከሩ፡በሐቅ፡መታገል፡ነው።ሕዝብ፡በረሃ ብ፡እያልለቀ፣እዬ፡ተሰደደ፣ሀገር፡እዬ፡ተሸጠ፣ገበሬው፡መሬቱን፡እዬ፡ተፈናቀለና፡የውጭ፡ዜጋ፡አምራቾች፡ምርታቸውን፡በቀጥታ፡ወደ፡አገራቸው፡እዬ፡ጫኑ፡ሲወስዱትና፡የበይ፡ተመልካች፡ለሆነው፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፣ብርሃኑ፡ነጋና፡አንዳርጋቸው፡ጽጌ፡አስተማማኝ፡የሚባል፡እርምጃ፡አልወሰዱም።ምንም፡የሠሩት፡ቁም፡ነገር፡የልለም።የሕልም፡እንጀራ፡እናበላሃልለን፡የሚሉት፡የጓደኞቸው፡አረመኔው፡አምባገነን፡ከሓዲ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ወያኔ፡ዘራፊ፡አስተዳደር፡ተብዬ፡ከቆሻሻ፡እዬ፡ለቀሙ፡እንዲበሉ፡ያደርረጋቸውን፡አይለውጠውም።

ኢትዮጵያና፡ሕዝቧን፡አጠንክሮ፡እግዚአብሐር፡ይባርክ።ሃሌ፡ሉያ።አሜን።

## ኢትዮጵያ፡ለዘላለም፡ትኖራልለች።ለይኩን፡ልይኩን፡አሜን።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ።
እ፡ጦማር፡- zienamarqos@yahoo.com